# ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት፡፡
# Ethiopia: The Kingdom of God Services

---

**ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፥**
**በሚገኙበት በማናቸውም ቦታና የኑሮ ዓይነት፥**
**በግለሰብ፥ በቤተሰብና በኅብረተሰብ አንድነት፡**
**በሓመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያንነት፥**
**በመንፈስ ቅዱስ ጸጋና በረከት በተሰበሰቡበት፥**
**በመስከረም አንድ ቀን፡ በርእሰ ዓውደ ዓመት፥**
**በድንግል ማርያም እና በኢየሱስ ክርስቶስ ልደታት፥**
**በእነርሱ የተገኘውን ዓመተ ምሕረት፥**
**በአዳምና ሔዋን፥ የዓለሙን ፍጥረት፥**
**በቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያን ነጻነት፥**
**ተቀብለው የጸኑባትን፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት፥**
**በታላቅ በዓልነት የሚያከብሩበት ሥርዓተ ጸሎት፡፡**

---

**በቅዱስ መስቀል ማኅተም ምልክትነት**
**በ፬ቱ ማዕዘን የሚፈጸም የቅዳሴ ሥርዓት፡፡**

**<u>፩ኛ፡ በምዕራቡ ማዕዘን፤</u>**

**ስለርእሰ ዓውደ ዓመተ ምሕረት፥**

**ምንባብ፡-**
**ሮሜ ምዕ. ፲፫፥ ቁ. ፰-፲፬፤**
**ራእ. ምዕ. ፳፩፥ ቁ. ፩-፰፤**
**ሓዋ. ምዕ. ፫፥ ቁ. ፲፱-፳፮፡፡**

**ምስባክ፡-** **መዝ. ፷፬፥ ቁ. ፲፩-፲፪፤**

| | |
|---|---|
| **ወትባርክ፡ አክሊለ ዓመተ ምሕረትከ፤** | **የምሕረትህን ርእሰ ዓውደ ዓመት፡ ትባርካለህ፤** |
| **ወይጸግቡ፡ ጠላተ ገዳም፤** | **ምድረ በዳው፡ በልምላሜ ይሸፈናል፤** |
| **ወይረውዩ፡ አድባረ በድው፡፡** | **የበረሃ ተራሮች፡ በዝናብ ይረካሉ፡፡** |

**ወንጌል፡-** **ሉቃ. ምዕ. ፬፥ ቁ. ፲፬-፳፱፡፡**

## ፪ኛ፡ በሰሜኑ ማዕዘን፤

### ስለቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያን ነጻነት፤

ምንባብ፡- ዕብ. ምዕ. ፯፥ ቁ. ፩-፲፤
ራእ. ምዕ. ፭፥ ቁ. ፩-፲፤
ሐዋ. ምዕ. ፰፥ ቁ. ፳፮-፴፱፤

ምስባክ፡- መዝ. ፷፯፥ ቁ. ፴፩-፴፪፤

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር፤
ነገሥተ ምድር፡ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር፤
ወዘምሩ ለአምላክነ፡፡

ኢትዮጵያ፡ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች፤
የምድር ገዢዎች፡ እግዚአብሔርን አመስግኑ፤
ለአምላካችንም ዘምሩ፡፡

ወንጌል፡- ማቴ. ምዕ. ፲፪፥ ቁ. ፴-፵፪፡፡

## ፫ኛ፡ በደቡቡ ማዕዘን፤

### ስለቅድስት ድንግል ማርያም

ምንባብ፡- ዕብ. ምዕ. ፱፥ ቁ. ፩-፭፤
ራእ. ምዕ. ፲፩፥ ቁ. ፲፭-፲፱፤
ሐዋ. ምዕ. ፩፥ ቁ. ፮-፲፬፡፡

ምስባክ፡- መዝ. ፻፴፩፥ ቁ. ፲፫-፲፬፤

እስመ ኀረያ እግዚአብሔር ለጽዮን፤
ወኣብደራ፡ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ፤
ዛቲ ይእቲ፡ ምዕራፍየ ለዓለም፡፡

እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና፤
ማደሪያውም፡ ትኾነው ዘንድ ወዷታልና፤
"ይህች፡ ለዘለዓለም ማረፊያዬ ናት!" አለ፡፡

ወንጌል፡- ሉቃ. ምዕ. ፩፥ ቁ. ፳፮-፶፮፡፡

## ፬ኛ፡ በምሥራቁ ማዕዘን፤

### ስለኢየሱስ ክርስቶስ ልደት፤

የፍሬ ቅዳሴ፡

ምንባብ፡- ገላ. ምዕ. ፬፥ ቁ. ፩-፯፤
፩ኛ ዮሐ. ምዕ. ፬፥ ቁ. ፩-፲፭፤
ሐዋ. ምዕ. ፲፫፥ ቁ. ፲፮-፴፫፡፡

ምስባክ፡- መዝ. ፪፥ ቁ. ፯-፰፤

እግዚአብሔር ይቤለኒ ወልድየ አንተ፤
ወአነ ዮም ወለድኩከ፤
ሰኣል እምኔየ፡ እሁበከ አሕዛበ ለርስትከ፡፡

እግዚአብሔር አለኝ፡ "አንተ ልጄ ነህ!"
እኔ፡ ዛሬ ወለድሁህ፤
ለምነኝ! አሕዛብን፡ ለርስትህ እሰጥሃለሁ፡፡

ወንጌል፡- ሉቃ. ምዕ. ፪፥ ቁ. ፩-፳፡፡

# <u>የልደት ዝማሬ</u>

አማን፡ በአማን፡ አማን፡ በአማን፤ አማን፡ በአማን፡ አማን፡ በአማን፤

መንክር ስብሓተ ልደቱ! መንክር ስብሓተ ልደቱ::

## <u>ትርጉም</u>

እውነት በእውነት! እውነት በእውነት ! እውነት በእውነት! እውነት በእውነት !

የክርስቶስ የልደቱ ገናናነት ዕፁብ ድንቅ ነው! የክርስቶስ የልደቱ ገናናነት ዕፁብ ድንቅ ነው!

# <u>የምሥራች ሰላምታ</u>

በዚህ በዓልና ከዚህ ቀን ጀምሮ፡ እስከ በዓለ ግዝረቱ፥ ከዚያም፡ እስከ በዓለ በአተ መቅደሱ ድረስ፡ ካህናትና ምእመናን፥ እርስ በርሳቸውም የሚለዋወጡት የምሥራች ቃል፡-

ከመስከረም ፩ እስከ ፳ ቀን፡-

*"ዮም ፍሥሓ ኮነ!"* *"በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ!"*
"ዛሬ ደስታ ኾነ!" "የክርስቶስ የልደቱ በዓል ነውና!"

ከመስከረም ፳ እስከጥቅምት ፲ ቀን፡-

*"ዮም ፍሥሓ ኮነ!"* *"በእንተ ግዝረቱ ለክርስቶስ!"*
"ዛሬ ደስታ ኾነ!" "የክርስቶስ የግዝረቱ በዓል ነውና!"

በጥቅምት ፲ ቀን፡-

*"ዮም ፍሥሓ ኮነ!"* *"በእንተ በአተ መቅደሱ ለክርስቶስ!"*
"ዛሬ ደስታ ኾነ!" "ክርስቶስ፡ ወደቤተ መቅደስ የገባበት ቀን ነውና!"

ይህ የደስታ መንፈስና ሥርዓት፡ እስከጥቅምት ፲ ቀን ይቀጥላል::

---